የባለአክሲዮኖች 5ኛ መደበኛ እና 2ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ

በኢፌዲሪ የንግድ ሕግ አንቀፅ 366(1)፣ 367(1) እና 370 እንዲሁም በባንካችን መመስረቻ ጽሁፍ አንቀፅ 12.1.6 መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 9.1 መሰረት አማራ ባንክ አክሲዮን ማህበር የባለአክሲዮኖች 5ኛ ዓመታዊ መደበኛ እና 2ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ዕሁድ ህዳር 27 ቀን 2019 ዓ.ም ከጠዋቱ 2:00 ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ ጃንሜዳ ይካሔዳል። በመሆኑም የተከበራችሁ የባንካችን ባለአክሲዮኖች በዕለቱ በጉባዔው ላይ እንድትገኙልን የአማራ ባንክ አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል።

1. ባንኩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች
   - **1.1.** የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ፡-
     አዲስ አበባ፣ ቂርቆስ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 8፣ ለገሃር መብራት - አመልድ ሕንጻ ከ14-25ኛ ፎቅ
     ስልክ: የጥሪ ማዕከል: 690 ፖ.ሳ.ቁ: 28450 ኮድ 1000
     ድረ ገጽ: https://amharabank.com.et/
   - **1.2.** የአክሲዮን ማህበሩ የምዝገባ ቁጥር፡- MT/AA/3/0052689/2014
   - **1.3.** የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ብር፡- 7,498,925,000
   - **1.4.** የአክሲዮን ማህበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ብር፡- 7,498,925,000

2. **የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች፡-**
   - **2.1.** የዳይሬክተሮች ቦርድ እጩ ቅበላ እና ምርጫ አስፈፃሚ ጊዜያዊ ኮሚቴ መምረጥ፣
   - **2.2.** በ2025/26 የተደረጉ የአክሲዮን ዝውውሮችን ማፅደቅና አዳዲስ ባለአክሲዮኖችን መቀበል፣
   - **2.3.** እ.ኤ.አ የ2025/26 የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ማድመጥና ተወያይቶ ማፅደቅ ፣
   - **2.4.** እ.ኤ.አ የ2025/26 የባንኩን የውጭ ኦዲተር ሪፖርት ማድመጥና ተወያይቶ ማፅደቅ ፣
   - **2.5.** እ.ኤ.አ የ2026/2027፣ 2027/2028 እና 2028/2029 የባንኩን ሂሳብ የሚመረምሩ የውጭ ኦዲተር መሾምና የአገልግሎት ዋጋ ማፅደቅ፤
   - **2.6.** ባንኩን ለቀጣይ 3(ሶስት) ዓመታት የሚመሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫን ማካሄድ፣
   - **2.7.** እ.ኤ.አ የ2025/26 የትርፍ ድርሻ ድልድል እና ክፍፍልን በተመለከተ የዳይሬክተሮች ቦርድ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ማዳመጥና ተዋያይቶ ማፅደቅ፣
   - **2.8.** የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን እ.ኤ.አ የ2025/26 ዓመታዊ የስራ ዋጋ እና እ.ኤ.አ የ2026/2027 ወርሃዊ አበል በሚመለከት በቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተወያይቶ ማፅደቅ ናቸው።

3. **የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች**
   - **3.1.** ተሻሽሎ በቀረበው የባንኩ መመስረቻ ጽሑፍ ላይ ተወያይቶ ማፅደቅ፣
   - **3.2.** የባንኩን የካፒታል መጠን ማሳደግ አስመልክቶ በቀረበው አጀንዳ ላይ ተወያይቶ ማፅደቅ።

ማሳሰቢያ ፤-

1. በጉባዔው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ በተሰጠ ውክልና ወይም በንግድ ሕጉ አንቀፅ 377 መሰረት ጉባዔው ከሚካሔድበት ቀን 3(ሶስት) ቀናት በፊት በየትኛውም የባንኩ ቅርንጫፍ ማንነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውንና ኮፒ ይዘው በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በባንኩ የተዘጋጀውን ውክልና ቅፅ ሞልተው በመፈረም ተወካይ በመሾም በጉባዔው ተካፋይ ለመሆንና ድምፅ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን። ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ በተሰጠ ውክልና በጉባዔው ላይ የሚሳተፉ ተወካዮች በጉባዔው ቀን የውክልናውን ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል።
2. ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን በባንኩ ጠቅላላ ጉባዔ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ነው። እንዲሁም በስራ ላይ ያሉ የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና የባንኩ ሰራተኞች ዋና ስራ አስፈፃሚን እና ከፍተኛ ኃላፊዎችን ጨምሮ ባለአክሲዮኖችን በመወከል በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር SBB/91/2024 አንቀፅ 20.3 መሰረት በጉባዔ ላይ መሳተፍ የማይችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን።
3. ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባዔው ላይ ለመሳተፍ ስትመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታችሁን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ብሔራዊ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውንና ፎቶ ኮፒ በመያዝ በጉባዔው ላይ መሳተፍ ይችላሉ። እንዲሁም ትውለደ-ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው የባንካችን ባለአክሲዮኖች ትውልደ-ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት መታወቂያ (ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እንገልፃለን።
4. ባለአክስዮኖች ባስመዘገቡት ተንቀሳቃሽ /ሞባይል ስልክ ቁጥር ላይ የባለአክስዮን መለያ ቁጥር የሚላክ በመሆኑ ባለአክስዮኖች ወይም ተወካዮች ባንኩ ባዘጋጀው ቅፅ ውክልና ለመስጠትም ሆነ ወደጉባዔው ሲመጡ ይህንኑ መለያ ቁጥር ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል።
5. ድርጅትን ወክሎ የሚቀርብ ተወካይ የድርጅቱ/የማህበሩ ስራ አስኪያጅ መሆኑንና ድርጅቱን/ማህበሩን ወክሎ በጉባዔ ላይ ድምፅ ለመስጠት የሚያስችል ስልጣን ያለው ስለመሆኑ የሚያሳይ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት የተመዘገበ የመመስረቻ ፅሁፍ ወይም መተዳደሪያ ደንብ ወይም ቃለ-ጉባዔ በማስረጃነት ይዞ መቅረብ አለበት ፣ አልያም በባንኩ የውክልና ቅጽ መሰረት ውክልና የተሰጠው መሆን አለበት።
6. ባንኩ ባዘጋጀው ቅፅ ውክልና ለምትሰጡ ባለአክስዮኖች ሁሉም የባንኩ ቅርንጫፎች በስራ ቀናቶች የሚያስተናግዱ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን።

ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥሮች +251115581461 ወይም +251115583198 ይደውሉ።

የአማራ ባንክ አ.ማ
የዳይሬክተሮች ቦርድ